# ሰባቱ ምሥጢራት ቤተክርስቲያን

እነዚህ ሰባቱ ምሥጢራት ቤተክርስቲያን በዓይን የማይታይ በእጅ የማይዳሰስ የመንፈስ ቅዱስ ለምዕመናን የሚታደልባቸው የሚፈጽምባቸው ናቸው። ምሥጢር ለወዳጅ የሚነገር እንደሆነ ሁሉ እነዚህም ምሥጢራት መባለቸው ለእውነተኛ ክርስቲያኖች የሚፈጸሙ በመሆናቸው ነው።

ዝርዝራቸውም፦ 1. ጥምቀት
2. ሜሮን
3. ቁርባን
4. ክህነት
5. ተክሊል
6. ንስሀ
7. ቀንዲል ሲሆን አፈጻጸማቸውም ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

1. ጥምቀት ይህ የሚፈጸመው ለሚያምን ሰው ነው። ማር. 16፥16 ቤተክርስርቲያናችን የምታጠምቀው የሚያመኑ የክርስቲያን ልጆች ከሆኑ ወንድን በ40 ቀን ሴት ልጅን ደግሞ በ80 ቀን ነው። (ምስጢረ ጥምቀትን ይመልከቱ) የክርስቲያን ቤተሰብ ያልሆኑ ግን በዚህ ዕድሜ አይጠመቁም አስቀድሞ ትምህረተ ክርስትና ተምረው ከዓመት በኋላ ነው። ህፃናት ሲጠመቁ የክርስትና አባት ወይም የክርስትና እናት ይደረጋል። ይህም ህጻናቱን የሃይማኖት ትምህርት ያስተምሩ ዘንድ ነው።

ህፃኑም ይሁን ትልቅ ሰው በሚጠመቁበት ጊዜ 3 ጊዜ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ካሰገደ በኋላ ካህኑ በሥላሴ ስም ያጥምቀዋል። ከዚህም ስጋውና ደሙን ይቀበላል።

- ጥምቀት የሚደረገው በውኃ ብቻ ነው፡
- ከተጠመቀ በኋላ ማተብ በአንገቱ ይታሰርለታል - ይህም ጌታን በጦር ሲወጉት ከጎኑ የፈሰሰው የደሙና የውኃው ምሳሌ ነው።
- ተጠማቂው 3 ጊዜ በውኃ ውስጥ ብቅ ጥልቅ ይደረጋል ወይም ካህኑ በላዩ ያፈስበታል። ምሳሌነቱ የጌታችን ሞቱ መቀበሩና ከሞት መነሳቱ ነው፡
- ጥምቀቱ ከመንፈስ ቅዱስ መወለድ ስለሆነ አንድ ጊዜ ብቻ ነው አይደገምም -

2. ሜሮን ይህ ቅዱስ ዘይት ሲሆን ማንኛውም ተጠማቂ ተጠምቆ ሲወጣ የሚቀባው ነው።ይህም የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ያሳድር ዘንድ ተጠማቂው በዚህ ይታተማል። ልክ እንደ ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ ይደረጋል።

3. ቁርባን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የዘላለም ሕይወት ይሆን ዘንድ ያቀረበው የራሱ ስጋና ደም ነው። ቄሱ ኅብስቱን በጸበል ወይኑን በጽዋዕ አድረጎ ሥርዓተ ቅዳሴው ሲያደርስ ወደ እውነተኛ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስጋና ደም ይለወጣል፡፤

- በሥርዓተ ቁርባን ጊዜ ቄሱ ስጋውን ያቀርባል ዲያቆን ደግሞ በዕረፈ መስቀል ደሙን
- ቁርባን የሚቆርበው ቢያንስ ለ15 ሰዓት ከምግብና መጠጥ ተከልክሎ ነው

- ስጋውና ደሙ (ቁርባን) ለክርስቲያን ሁሉ በንስሐ የተፈቀደ ነው

4. ክህነት ፦ በቤተክርስቲያናችን ሦስት ዓይነት የክህነት መዓረጋት አሉ።
   1. ዲያቆን፦ ይህም ከጋብቻ በፊት በአንብሮት ዕድ በጳጳሳት አማካኝት የሚሰጥ ነው።
   2. ቄስ ፦ አንድ ዲያቆን ሲያገባ ወይም ሲመነኩስ የሚሰጥ ሥልጣን ነው። ይህም በአንብሮት ዕድና በንፍሐት በጳጳሳት ይሾማል።
   3. ጳጳስ፦ ይህ ሹመት የሚሰጠው በድንግልና ላለ መነኩሴ ነው። የሚሾመው በመላ የሲኖዶስ አባላት ነው።

እነዚህ ያየናቸው የክህነት ሥልጣን የሚሰጡት ለአንድ ሰው አንዴ ብቻ ነው።

5. ተክሊል፦ በሁለት ክርስቲያኖች በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት ፈቃድ በቤተሰቦቻቸውም መልካም ፈቃድ ለሚደረግ ጋብቻ ቤተክርስቲያን የምትፈጽመው ሥርዓት ነው።
   - የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኝ መሆን አለባቸው
   - ደናግላን መሆን አለባቸው
   - በዝምድና ሰባት ትውልድ የራቁ መሆን አለባቸው
   - የሚፈጸመውም አንድ ጊዜ ብቻና በስጋወ ደሙ ነው

6. ንስሐ፦ አንድ ክርስቲያን በኃጢአት በሚወድቅበት ጊዜ ከእግዚአብሔር የሚጠይቀው ይቅርታ - መጸጸት፣ መመለስ፣ ከኃጢአትም መንጻት ፣ መጥራት ነው።
   - እያንዳንዱ ክርስቲያን መምህረ ንስሐ (የንስሐ አባት) ያስፈልገዋል
   - ንስሐ የሚደጋገም ነው። ኀጢአት ይደጋገማልና
   - ንስሐ አለ ብሎ ኀጢአትን መሥራት በእግዚአብሔር እንደመዘበት ይቆጠራል።

7. ቀንዲል፦ ይህ ሥርዓት ለስጋም ለነፍስም ለበሽተኞች የሚደረግ ነው። ይህም የታመሙ ሰዎች ጸሎት ተደረጎላቸው ቀንዲል ይቀባሉ ከህመማቸውም ይፈወሳሉ ከስጋ በሽታ ብቻም ሳይሆን ከነፍስ ደዌም ይድናሉ።

በጠቅላላው እነዚህ 7ቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን የሚፈጸሙበት እያንዳንዳቸው የራሳቸው የጸሎት አፈጻጸምና ሥርዓት አላቸው። እነዚህም የቤተክርስቲያኗ ሥርዐተ አምልኮ ማስፈጸሚያና የሃይማኖት መመሪያ ናቸው።